# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ሰኔ ፳፭ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ. ም
July 2, 2015

## ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ ልዩ ጉባኤ ተካሄደ

ተከፋፍሎ የነበረው ኢሕአፓ በሜሪላንድ ክፍለ ግዛት በባልቲሞር ከተማ ለሦስት ቀናት ያካሄደው የአንድነት ልዩ ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀቀ።

ከአንድ ቀን በፊት ከተደረገው ሕዝባዊ ሲምፖዚዬም ተከትሎ ከሰኔ ፳፩ እስከ ሰኔ ፳፬ ቀን ፪ ሺ ፯ ዓ ም (June 28 - July 1, 2015) በተካሄደው ልዩ ጉባዔ ከመላው ዓለም የመጡ አባላት የተሳተፉበት ነበር።

ይህ ጉባዔ የድርጅቱን ዋና ዋና ጉዳዮች እንዲሁም በድርጅቱ ውስጥ ተፈጥሮ የነበረውን ችግርና ለመለያየት የነበሩትን ምክንያቶች በሰፊው ከመረመረ በኋላ ችግሮችን አስወግዶ በአንድነት ለመታገል ወስኗል። ይህንን ልዩ ታሪካዊ የአንድነት ጉባዔ ግምት ውስጥ በማስገባት የድርጅቱ መጠሪያ ስም ኢሕአፓ (አንድነት) እንዲሆን ወስኗል።

ጉባዔው የኢትዮጵያን አጠቃላይ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት ከገመገመ በኋላ፤

- ሀገሪቱ በአንድ ብሄርተኛ አምባገነን ቡድን ሥር በመውደቋ ምክንያት ሕዝባችን የቀን ተቀን ሕይወቱ አደጋ ላይ የወደቀ መሆኑን፣
- በሀገሪቱ ውስጥ መሠረታዊ የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች የተረገጡ መሆናቸውን፤ እነዚህ መሠረታዊ፤ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በጠፉበት

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**

**Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ሁኔታ ነፃ፤ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሊካሄድ የሚችልበት ሁኔታ አለመኖሩን፤ ይህንንም እውነታ ፪ ሺ ፯ ዓ. ም ምርጫ ተብዬ እንደገና እውነታውን ማጋለጡን፣

- ይህ አምባገንነን የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ በፈጠረው ሁኔታ ምክንያት ሀገራችን በጎሣ፣ ፖለቲካና በውጭ አክራሪ ኃይሎች ተጽዕኖ ከፍተኛ አደጋ ላይ መሆኗን፣
- ዜጎች ለረዥም ዘመን ሃብትና ንብረት አፍርተው ከኖሩበት ቦታ መፈናቀላቸውን፣
- በሀገሪቱ የዕምነት ነፃነት መጥፋቱን፤
- አገዛዙ በጎረቤት አገሮች ጣልቃ በመግባቱ ምክንያት አክራሪነት በሀገራችን እንዲያንዣብብ አንዱ ምክንያት መሆኑን፣
- ወያኔ/ኢህአዴግ የሀገሪቱን ዋና ዋና የኤኮኖሚ ዘርፎች በፓርቲው መዳፍ ሥር አውሎ ዜጎች በነፃነት በኤኮኖሚው መስክ ተሳትፎ እንዳያደርጉ መደረጉን፣
- አገዛዙ ኤኮኖሚው በሁለት አሃዝ አድጓል ይበል እንጂ፣ እውነታው የሚያሳየን ግን ድህነት መንሰራፋቱን፤ አብዛኛው ሕዝባችን ጠዋት በልቶ ማታ አለመድገሙን፤ ለኑሮ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች በብቃት አለመገኘታቸውንና ዋጋቸው እጅግ መናሩን፣
- በሀገሪቱ ውስጥ በሥራ ማጣትና በኑሮ ዋስትና እጦት ምክንያት ከሀገራቸው እየተሰደዱ በባዕድ አገር ለሞትና ለዘመናዊ ባርነት የሚዳረጉ ወጣቶች ለስደታቸው ምክንያት የሆነው አምባገነኑ የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ አስተዳደራዊ ብልሹነት መሆኑን ፣
- ከስልሳዎቹ በፊት ጀምሮ አርሶ አደሩ የመሬት ባለቤት እንዲሆን ብዙ መሥዋዕትነት የከፈለ ቢሆንም አሁንም አርሶ አደሩ የአገዛዙ ገባር መሆኑንና በመሬት ጥበት ምክንያት ከቀየው እየተፈናቀለ ወደ ከተማ እየጎረፈ መሆኑን፣
- የውጭ ባለሃብቶች የአገሪቱን ሃብት ከመዝረፍ በተጨማሪ ደሪውን ሕዝብ ከቀየው በማፈናቀል ችግር ላይ እንዲወድቅ ማድረጋቸው፣
- የውጭ ባለሃብቶች ያለምንም ቁጥጥር የአገሪቱን የተፈጥሮ ደን በማውደም ሀገራችን ወደ በረሃነት እንድትለወጥ ማድረጋቸው፣
- አገዛዙ አያት ቅድማያቶቻችን ጠብቀው ያኖሯትን አገር ቆርሶ ለባዕዳን መስጠቱን፣

- ህገ-መንግሥታዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን በመጠቀም በሕጋዊ መንገድ ለመጋገል የሞከሩ ዜጎች በየቦታው እየተለቀሙና እየታደኑ ወደ እሥር ቤት መወርወራቸውን፣
- በቅርቡ የተደረገውን የምርጫ ቲያትር ተከትሎ በርካታ የተቃዋሚ አባላትን በጠራራ ፀሐይ በአገዛዙ የስለላ መረብ አማካኝነት መገደላቸው የአገዛዙን አምባገነንነትና ፀረ-ዴሞክራሲነት በግልጽ የሚያመለክት መሆኑን በማመን የአንድነት ጉባዔው ይህንን አረመኔያዊ ድርጊት አውግዟል።

ጉባዔው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ከመረመረና ግንዛቤ ከወሰደ በኋላ፤

- ጉባዔው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ሀገር አፍራሽና አጥፊ ፖሊሲዎቹን በጥብቅ አውግዟል።
- ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት፣ የወያኔ/ኢህአዴግን አገዛዝ ማስወገድ እንደሚገባ አረጋግጦ የበለጠ ተጠናክሮ መታገል እንደሚገባ በድጋሚ አረጋግጧል።
- ይህን ለማስፈጸም ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች የዴሞክራሲ ንቅናቄዎች ጋር በመተባበር መሥራት አስፈላጊ መሆኑ አጽዕኖት ሰጥቶበታል፤ ከዚህ አኳያም ኢሕአፓ (አንድነት) በኢትዮጵያ ሕዝብ የጋር ትግል ሸንጎ ውስጥ በአባልነት ለመቀጠል ወስኗል።

በመጨረሻም የአንድነቱ ጉባዔ የፓርቲውን የምክር ቤት የአመራር አባላትና የመብት አስጠባቂ ኮሚሽን አባላትን መርጦ ጉባዔው በተሳካ ሁኔታ ተጠናቅቋል።

የተባበረ ትግል ምንጊዜም አቸናፊ ነው!